MORESH WEGENIE AMARA ORGANIZATION
ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት

P. O. Box 55321, Washington, DC 20040-5321
Tel: (202)-677-0094
Web: http//www.moreshwegenie.org/

ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት   እሑድ ሐምሌ ፲፯ ቀን ፳፻፰ ዓ.ም.   ቅፅ ፬ ፣ ቁጥር ፲፯

# የሞረሽ ወገኔ ዐማራ ድርጅት የማዕከላዊ ምክርቤት 8ኛ መደበኛ ስብሰባ

## <u>የአቋም መግለጫ</u>

እኛ የሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ማዕከላዊ ምክር ቤት አባሎች፣ በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የማዕከላዊ ምክርቤቱን 8ኛ መደበኛ ስብሰባ ቅዳሜ ሰኔ 25 ቀን 2008 ዓ.ም. (Saturday July 2, 2016) አድርገናል። ምክር ቤቱ፦

**<u>አንደኛ</u>፦** በሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ሊቀመንበር የቀረበውን የማዕከላዊ ምክር ቤቱን የስድስት ወር የሥራ ሪፖርት አዳምጠን በሙሉ ድምፅ አጽድቀናል።

**<u>ሁለተኛ</u>**፦ በሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት የቁጥጥርና ፍተሻ ኮሚቴ ሊቀመንበር የቀረበውን የስድስት ወር የገንዘብ አጠቃቀምና አያያዝ፣ እንዲሁም የሥራ አፈጻጸም ምዘና ሪፖርት አዳምጠናል፤ የሪፖርቱን ገንቢ አቀራረብ አመሥግነናል።

**<u>ሦስተኛ</u>፦** በአኅጉሮችና አገሮች በተደራጁት የሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ምክር ቤቶችና ኮሚቴዎች ተጠሪዎች አማካይነት የቀረቡትን ሪፖርቶች አዳምጠን ለወደፊትም ሊበረታታ የሚገባው አሠራር መሆኑን ተስማምተናል።

**<u>አራተኛ</u>**፦ የአባላትን ቁጥር ለመጨመር እና ለሞረሽ-ዐማራ የሬድዮ ፕሮጀክት ገንዘብ ለማሰባሰብ እንዲያስችል፣ በተለያዩ ከተሞች ሕዝባዊ ስብሰባዎችን ማካሄድ ወሣኝ መሆኑን ሙሉ ስምምነት ላይ ደርሰናል።

በጉባኤያችን ወቅት በቀረቡት ሪፖርቶች መነሻነት ድርጅቱ የቆመለትን ዓላማ በማሳካት ረገድ አካላትና አባላት ምን ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው በስፋት ተወያይተን በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የአቋም መግለጫ አውጥተናል።

### 1. «ሞረሽ የዐማራ ድምፅ» የሬዲዮ ጣቢያን ሥራ ስለማስጀመር፥

ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት፣ የዐማራን ነገድ ከፈጽሞ ጥፋት የመታደግና ድምፅ አልባ ለሆነው ዐማራ ድምፅ ለመሆን ለቆመለት ዓላማ ስኬት ዕውን መሆን፣ የዐማራው ድምፅ ከአጽናፍ አጽናፍ እንዲያስተጋባ ለማድረግ፣ እንዲሁም የዓለም ማኅበረሰብ በዝምታ፣ የነገዱ ምሁራን ደግሞ በቸልታ የሚመለከቱት የዘር ጥፋትና የዘር ጽዳት ወንጀል እንዲቆም፣ ወንጀለኞች ለፍትሕ እንዲቀርቡ እገዛና ድምፅ የሚሆን **«ሞረሽ የዐማራ ድምፅ»** የተሰኘ የሬዲዮ ጣቢያ ለመጀመር በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛል። ይህ የሬድዮ ጣቢያ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ተጨማሪ አማራጭ የመረጃ ምንጭ ከመሆን ባሻገር፣ ድምፁ ለታፈነው የዐማራው ነገድ ልሣን እና አንደበት በመሆን፣ ሕዝብን ለማንቂያ፣ ለማስተማሪያ፣ ለማሳወቂያና ለማደራጃነት ጉልህ ሚና ሊጫዎት እንደሚችል ምክርቤቱ አምኖበታል። በዚህ ረገድ እስካሁን የሬዲዮኑን ፕሮግራም ለማስጀመርና ሥራውን ለማስመቀጠል የተደረጉት ጥረቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ፣ ለሬዲዮው መርኃግብር መጀመር ወሣኝ የሆነው የገንዘብ ድጋፍ በማያቋርጥ መልኩ እንዲመነጭ፣ ልዩ ልዩ የገቢ ምንጮችን በመጠቀም የገንዘብ አቅሙን ለማጎልበት አካላትና አባላት የምችለውን ሁሉ ለማድረግ ቃል እንገባለን። ከሁሉም በላይ ገቢው አስተማማኝ የሚሆነው የሬዲዮኑ ደጋፊዎች በቋሚ አባልነት የቻሉትን ያህል በየወሩ ያላንዳች ጎትጓች መክፈል ሲችሉ ስለሆነ፣ በዚህ ረገድ ከራሳችን ጀምረን በየአካባቢያችን የሚኖረውን ዐማራ የሆነውን ብቻ ሳይሆን፣ ሰብአዊነት የሚሰማቸውን ሰዎች ሁሉ ስለ«ሞረሽ የዐማራ ድምፅ ሬዲዮ» ዓላማ በማሳወቅ የገቢ ምንጩ አስተማማኝ እንዲሆን የየበኩላችን ሳንታክትና ሳንሰለች በትጋት ለመሥራት ዝግጁነታችን በድጋሚ እናረጋግጣለን።

**2. «ምጽአተ ዐማራ፤ ተገድሎና ተገዳድሎ የማያልቅ፣ ተነቅሎ የማይደርቅ» በተሰኘ ርዕስ ስለሚታተመው መጽሐፍ፡-**

አንድ ሕዝብ ታሪኩን፣ ባህሉን፣ ኃይማኖቱንና ማንነቱን አስጠብቆ ለተከታታይ ትውልድ ማሸጋገር የሚችለው፣ የእርሱ ተቃራኒ ከሆኑ የጥፋት ኃይሎች ራሱን መጠበቅና መከላከል ሲችል እንደሆነ ይታመናል። ለዚህም ዋናው ሥራ ትውልዱ ባህሉን፣ ቋንቋውን፣ ኃይማኖቱን፣ ታሪኩን፣ ዕሴቶቹን፣ በአጠቃላይ ማንነቱን በቅጡ እንዲያውቅ ሲደረግ ነው። ትውልዱ ወዳጅና ጠላቱን የሚለይበት፣ ከተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር የተጣጣመ የታሪክ ግንዛቤ በተከታታይ እንዲጨብጥ መሠረታዊ ዕውቀት ሊጨብጥ ይገባዋል። በዚህ ረገድ ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት፣ የዐማራው ነገድ ለኢትዮጵያ አንድነት ዳብሮ መቀጠልና ለነፃ አገርነትና መንግሥትነት በየትውልዱ የከፈለውን መተኪያ የሌለው የሕይዎት ዋጋ፣ በአንፃሩ ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ዐማራ የሆኑ ቡድኖችና ግለሰቦች ዐማራውን ታሪኩንና ማንነቱን ጥላሸት ከመቀባት አልፈው፣ የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ወንጀል እንደሚጽሙበት ዓለም ያወቀው ገሃድ ሃቅ ነው። በዛሬው ዘመን ግን የዐማራው ነገድ ትውልድ ዕውነታውን ባለማወቁ በአባቶቹ ማንነትና ታሪክ ከማፈር አልፎ፣ እንዲሸማቀቅና ከማንነቱ የመራቅ አዝማሚያ እንዲያሳይ እንዳስገደደው እየተስተዋለ ነው። ይህን አዝማሚያ የሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት አጥብቆ ከሚዋጋቸው ጉዳዮች አንዱና ዋናው በመሆኑ፣ የዐማራው ወጣት ትውልድ በአባቶቹ ማንነትና ታሪክ የሚመካና የሚኮራ እንዲሆን፣ ይህንም አስጠብቆ ለትውልድ እንዲያሸጋግር፣ የዐማራውን ማንነት፣ ታሪክና ለኢትዮጵያውነት የከፈለውን መስዋዕትነት የሚያሳይ፣ ከ1500 እስከ 2008 ዓ.ም. ባሉት የ508 ዓመታት ታሪክ ውስጥ፣ ዐማራው የተጫወተውን አኩሪ ሚና እና «ጠላታችን ነው» ብለው በፈረጁት ኃይሎች የተፈጸመበትንና የሚፈጸምበትን የዘር ጥቃት ስፋትና ጥልቀት የሚያሳይ፣ **«ምጽአተ ዐማራ፤ ተገድሎና ተገዳድሎ የማያልቅ፣ ተነቅሎ የማይደርቅ»** በተሰኘ ርዕስ ባለፉት ዓመታት ሲዘጋጅ የነበረው መጽሐፍ ተጠናቆ በቅርቡ ለገበያ ይቀርባል። በመሆኑም የሞረሽ ወገኔ አካላትና አባላት ይህን መጽሐፍ ለዐማራው ነገድ አባሎች በማሰራጨት፣ ዐማራው በመረጃ የታገዘ የተጠናከረ ትግሉን እንዲያፋፍም የምንችለውን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁነታችን እናረጋግጣለን።

**3. አዳዲስ አባላትን ስለመመልመል እና የድርጅታችንን መዋቅር ስለማጠናከር፡-**

ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት የቆመለትን የዐማራን ነገድ ኅልውና አስጠብቆ፣ የኢትዮጵያን ትንሣዔ ለማብሰር ለሚያደርገው ውስብስብ ትግል፥ የጊዜ፣ የዕውቀት፣ የመረጃ እና የሰው ኃይል በበቂ መጠን መገኘትን ይጠይቃል። የእነዚህ ሁሉ ብቸኛው ምንጭ ደግሞ ሰው ነው። ሰው ካለ ገንዘብ፣ ዕውቀት፣ መረጃ፣ ጊዜ አለ። ስለሆነም እያንዳንዱ የሞረሽ ወገኔ ዐማራ ድርጅት አካልና አባል፣ በሚኖርበት እና በሚሠራበት አካባቢ የሚኖሩ ዐማሮችን ማንነት እያጠና ሞረሽ ወገኔን እንዲቀላቀሉ የማድረግ የምልመላና የማደራጀት ሥራ ከሁሉም ሥራዎቻችን ቅድሚያ በመስጠት ሞረሽ ወገኔን በሰው ኃይል ለማጠናከር ያለንን ሁለንተናዊ አቅም በሥራ ላይ ለማዋል እንጥራለን።

ዐማራን ከፈጽሞ ጥፋት እንታደጋለን!

ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃልኪዳን ነው!

**ቅዳሜ ሰኔ ፳፱ ቀን ፪ሺህ፰ ዓም (Saturday July 8, 2016)**

**ዋሽንግተን ዲሲ**